አፍሪካ ቲቪ

10

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት አዝካር ፣ ዱዓዕ እና ከፍተኛ ምንዳ ያላቸው ሥራዎች

5

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

| | ተግባሩ | ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የተነገረለት መረጃው |
|---|---|---|
| 20 | በአንደኛ ሶፍ ላይ ሶላት መስገድ | ሰዎች በአዛንና በአንደኛ ሰልፍ ያለው ምንዳ ምን እንደሆነ ቢያዉቁና በእጣ ካልሆነ በስተቀር የማይገኝ ቢሆን እንኳን እጣ ይጣጣሉ ነበር፡፡ |
| 21 | ራቲባ ሱናዎችን ጠብቆ መስገድ | በሌትና በቀን አስራ ሁለት ረከዓዎችን የሰገደ ሰው በጀነት ቤትይሰራለታል፡፡ እነሱም አራት ከዙህር በፊት፤ ሁለት ረከዐ በኋላ፤ ሁለት ረከዐ ከመግሪብ በኋላ፤ ሁለት ረከዐ ከዒሻ በኋላ፤ ሁለት ረከዐ ከሱብሂ በፊት ናቸው፡፡ |
| 22 | ትርፍ ሶላቶችን ማብዛት | ለአላህ ሱጁድ አብዛ፤ ምክኒያቱም ለአላህ አንድም ሱጁድ አታደርግም፣ በየ ሱጁዱ ደረጃህን ያሳደገና ወንጀልክንም የሰረዘልህ ቢሆን እንጂ፡፡ |
| 23 | የሱብሂ ዋናው ሶላትና ሱናው ሶላት | የሱብሂ ሱናዎች ከዱንያና በሷ ውስጥ ካሉ ነገሮች ሁሉ ይበልጣሉ፡፡ የሱብሂን ግዴታ (ፈርድ) ሶላትን የሰገደ በአላህ ጥበቃ ስር ነው፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| **24** | የዱሓ ሶላት | በእያንዳንዳችሁ አካል ላይ ሶደቃ አለባችሁ። አንዷት ሱብሀነላህ ሶደቃ ናት። አንዷት አልሐምዱሊላህ ሶደቃ ናት። አንዷት ላኢላሀ ኢለሏህ ሶደቃ ናት። አንዷት አላሁ አክበር ሶደቃ ናት። በደግ ነገር ማዘዝ ሶደቃ ናት። ከመጥፎ ነገር መከልከል ሶደቃ ናት። ነገር ግን ከዚህ ሁሉ የዱሃ ሁለት ረከዓ ሶላቶች ይበቁታል። |
| **25** | አላህን እያወሳ በመስገጃው ላይ የተቀመጠ | ከመስገጃው ላይ ተቀመጦ ውዱዕ ሳይፈታ ያለ ሰጋጅ ሁሉ መላይኮች አላሁመ ግፊር ለሁ አላሁመ ርሀምሁ ይሉለታል። |
| **26** | ሱብሂን በጀማዐ ሰግዶ ፀሐይ ዕስከምትወጣ ድረስ በዚክር ቆይቶ ሁለት ረከዐ መስገድ | ሱብሂን በጀማዐ ሰግዶ ፀሐይ እስከምትወጣ ድረስ በዚክር ቆይቶ ሁለት ረከዐ የሰገደ ሰው ሙሉ ሐጅና ሙሉ ዑምራ እንዳደረገ ይቆጠራል። |
| **27** | ሌሊት ለሶላት የነቃና ሚስቱን ያነቃ | ሌሊት ለሶላት የነቃ፤ ሚስቱን ያነቃና አብረው ሁለት ረከዓ የሰገዱ ከሆነ አላህን ከሚያወሱት ውስጥ ይመደባሉ። |

| | | |
|---|---|---|
| 28 | ሌሊት ለመስገድ አስቦ እንቅልፍ የጣለው ሰው | ሌሊት ለሶላት የነቃ፤ ሚስቱን ያነቃና አብረው ሁለት ረከዐ የሰገዱ ከሆነ አላህን ከሚያወሱት ውስጥ ይመደባሉ፡፡ |
| 29 | ገበያ የገባ ሰው የሚያደርገው ዚክር | ላኢላሀ ኢለሏህ ወህደሁ ላሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልኩ ወለሁል ሐምዱወሁወ ዩህዪ ወዩሚቱ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢንቀዲር...) ያለ ሰው ሚሊዮን መልካም ስራ ይፃፍለታል፡፡ ሚሊዮን ወንጀል ይታበስለታል፡፡ ሚሊዮን ደረጃም ይጨመርለታል፡፡ |
| 30 | ከሶላት በኋላ ሱብሃነ አላህ ወል ሀምዱ ሊላህ ወላሁ አክበር 33 ጊዜ ያለና በመጨረሻም ላኢላሀ ኢለሏህ ማለት | ከሶላት በኋላ ሰላሳ ሶስት ጊዜ ሱብሐነ አላህ፤ ሰላሳ ሶስት ጊዜ አልሐምዱሊላህ ሰላሳ ሶስት ጊዜ አላሁ አክበር ያለና መቶኛ ላኢላሀ ኢለሏህ ያለ ሰው ወንጀሉ የባህር ማዕበል ያህል እንኳን ቢሆን ይማርለታል፡፡ |
| 31 | ከሶላት በኋላ አየተል ኩርሲን ማንበብ | አንድ ሙስሊም ሙስሊም ወንድሙን ከጎበኘ አንድ ሺህ መላዒካ እስከ ማታ ድረስ ዱዓ ያደርጉለታል፡፡ ማታ ካየው ደግሞ አንድ ሺህ መላዒካ እስከ ጧት ድረስ ዱዓ ያደርጉለታል፡፡ |

| | | |
|---|---|---|
| 32 | በሽተኛን መጠየቅ (ማየት) | አንድ ሙስሊም ሙስሊም ወንድሙን ከጎበኘ አንድ ሺህ መላይካ እስከ ማታ ድረስ ዱዓ ያደርጉለታል፡፡ ማታ ካየው ደግሞ አንድ ሺህ መላዒካ እስከ ጧት ድረስ ዱዓ ያደርጉለታል፡፡ |
| 33 | ችግር የደረሰበት (ፈተና ላይ የወደቀን) ሰው ያየ ሰው | አልሐምዱ ሊላህ አለዚ ዓፋኒ ሚሙብተላከ ቢሂ ወፈዶለኒ ዐላ ከሲሪን ሚመን ኸለቀ ተፍዲላ) ያለ ሰው ችግር አይነካውም፡፡ |
| 34 | ችግር የደረሰበትን ያፅናና | ችግረኛን ያፅናና ሰው ተመሳሳይ ምንዳ አለው፡፡ |
| 35 | በጀናዛ ላይ ሰግዶ አስከሚቀበር ድረስ የተከተለ (የሸኘ) | በጀናዛ አሸኛኘት ላይ ተገኝቶ እስኪሰገድበት የቆየ ሰው አንድ ቂራጥ ምንዳ አለው፡፡ ሰግዶ እስከሚቀበር ድረስ የተከተለ ሰው ሁለት ቂራጥ አለው፡፡ |



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

| | | |
|---|---|---|
| **36** | ለአላህ ብሎ መስጂድ የገነባ ወይም በግንባታ ላይ የተባበረ | የወፍ ጎጆ (የድንቢጥ ቤት) የሚያህል እንኳን ለአላህ ብሎ መስጂድ የገነባ ሰው በጀነት ቤት ይሰራለታል፡፡ |
| **37** | ገንዘብን ወጪ ማድረግ (መስጠት) | በየቀኑ ሁለት መላይካዎች ይወረዱና አንዱ ጌታዬ ለሰጠ ሰው ምትክ ስጠው፡፡ ሌላኛው ደግሞ የከለከለን አጥፋበት እያሉ ይለምናሉ፡፡ |
| **38** | ሰደቃ መስጠት | ሶደቃ ሀብትን (ገንዘብን) አታጎልም፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ይቅር ባይን ባሪያውን ክብር እንጂ ሌላ አይጨምርለትም፡፡ ለአላህ ብሎ  የተናነሰ ሰው አላህ ከፍ ያደርገዋል፡፡ (አንድ ድርሀም አንድ ሺ ዲርሀምን ቀደመች፡፡ ሲሉ እንዴት ሁኖ ነው የአላህ መልእክተኛ? ብለው ሲጠይቋቸው አንድ ሰው ሁለት ዲርሀሞች ነበሩትና አንዱን ሰጥቶ ሁለተኛውን ለራሱ ያስቀረ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ብዙ ንብረት ያለውና ከዚያም ንብረት ውስጥ አንስቶ አንድ ሺ ዲርሀም የሰጠ ማለት ነው አሉ፡፡ |
| **36** | ለአላህ ብሎ መስጂድ የገነባ ወይም በግንባታ ላይ የተባበረ | የወፍ ጎጆ (የድንቢጥ ቤት) የሚያህል እንኳን ለአላህ ብሎ መስጂድ የገነባ ሰው በጀነት ቤት ይሰራለታል፡፡ |